ክብርት ወ/ሮ ወርቅሰሙ ማሞ!

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ!

የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!

ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!

ክቡራትና ክቡራን!

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 እና አንቀፅ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልፅ ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ ይህን ሪፖርት አቀርባለሁ፡
2. በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን በ2011/2012 የኦዲት ዓመት ያከናወነው የ2010 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ እና የ2011 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ሂሳብ ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች የያዘ የኦዲት ሪፖርት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

## የ2010 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት፤

መ/ቤታችን በየበጀት ዓመቱ ተዘግቶ የሚቀርብለትን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት እያደረገ አስተያየት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት የ2010 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት ተጠናቆ ‹‹ከዚህ በስተቀር›› የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በግኝቶቹ ላይም የማስተካከያ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ት/ቢሮ በግብረ መልሱ ገልጧል፡፡ ዋና ዋና ግኝቶችም በዚህ ሪፖርት ቀርበዋል፡፡

### የገቢ ሂሳብ እቅድ ክንውን ሂሳብ

3. በ2010 በጀት ዓመት በዝክረ ህግ የታወጀ የገቢ እቅድ ብር 37,639,142,155.00 ሲሆን በቀረበው የሂሳብ መግለጫ የተሰበሰበ ገቢ ብር 37,040,021,993.14 ነው፡፡በዝክረ ህጉ ከታወጀው ክልሉ በራሱ አቅም የሚሰበስበው ገቢ ብር 11,206,231,266.00 ውስጥ ብር 10,551,339,987.15 የተሰበሰበ በመሆኑ በንፅፅር ሲታይ ብር 654,891,278.85 (5.84%) ከታቀደው ላይ ያልተሰበሰበ ሲሆን ከፌደራል መንግስት የድጎማ ገቢ በእቅዱ መሰረት ይሰበሰባል ተብሎ ከተያዘው ብር 24,847,273,372.00 ውስጥ የተሰበሰበው ብር 18,989,982,012.99 በመሆኑ በንጽጽር ሲታይ ብር 5,857,291,359.01(23.57%) ያልተሰበሰበ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ከእርዳታ ይሰበሰባል ተብሎ

ከታቀደው ብር 127,6347,517.00 ውስጥ ምንም አልተሰበሰበም፡፡ ይህም በገቢ አሰባሰብ ላይ ያለው አፈፃፀም ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ከዘላቂ ልት ግቦች ማስፈጸሚያ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ሂሳብ ብር 1,515,000,000.00 ውስጥ ብር 7,066,599,993.00 በመሰብሰቡ ብር 5,554,599,993.00 (23.57%) በብልጫ መሰብሰቡ አበረታች ሲሆን ከብድር ይሰበሰባል ተብሎ በእቅድ ያልተያዘ ቢሆንም ብር 432,100,000.00 መሰብሰቡ የበጀት ምንጭን ለማስፋት የተደረገው ጥረት አበረታች መሆኑን ያሳያል፡

በአጠቃላይ የክልሉ ገቢ የመሰብሰብ አቅሙ ከዓመት ዓመት እያደረገ የመጣ ቢሆንም በሌላ በኩል ወጪው በበለጠ ፍጥነት እየጨመረ ስለሆነ ክልሉ ወጭውን የመሸፈን አቅሙ 29.2% ላይ ስለሚገኝ አሁንም ገቢን በመሰብሰብ በኩል የሚመለከታቸው አካላት ርብርብ ሊያደርጉ እንደሚገባ ያመለክታል፡

**ያልተሰበሰበ /ያልተወራረደ፤ያልተወገደ/ የተሰብሳቢ ሂሳብ**

4. ሰኔ 30/2010 ላይ በክልሉ ውስጥ በአጠቃላይ የሚገኘው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 11,151,521,798.66 ሲሆን በዝርዝር ሲታይ ሂሳቡ በእድሜ ተተንትኖ ያልተያዘ በመሆኑ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ማረጋገጥና በ2009 በጀት ዓመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የተጨመረውን ለይቶ አስተያየት ለመስጠት የማያስችል ሲሆን በ2009 በጀት አመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በብር 1,264,725,726.69 /12.79%/ እድገት ያሳያል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ3 ቢሮዎች የተያዘው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት( SDG) የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 977,826,677.56 /21.88%/ ሲሆን ይህም በ2009 በጀት ዓመት ከነበረው የSDG ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,163,454,872.95 ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በ1,185,628,195.39 (55%) የቀነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለሆነም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ አዝጋሚ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠውና ሂሳቡ በዕድሜ ተተንትኖ እንዲሰራ ሆኖ መወራረድ የሚችለውን ሂሳብ ማወራረድ እንዳለበትና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊሰበሰብ የማይችለውን ደግሞ ቀደም ሲል በወጣው የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝና አሰራረዝ መመሪያ መሰረት መፈጸም እንደሚገባ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

**ለሚመለከተው ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ**

5. በሰኔ 30/2010 ላይ በክልሉ ውስጥ በአጠቃላይ የሚገኘው የተከፋይ ሂሳብ ብር 6,034,134,303.19 ሲሆን ይህ ሂሳብ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየና በ2009 በጀት ዓመት ተይዞ ከነበረው የተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደና በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጨመረውን በመለየት አስተያየት ለመስጠት በሚያስችል መንገድ አልተያዘም፡፡ የ2010 በጀት አመት የተከፋይ ሂሳብ በ2009 በጀት አመት ከነበረው ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በብር 219,380,996.61 /13.77%/ እድገት አሳይቷል፡፡

ስለሆነም የደመወዝ ተከፋይ፣ የጡረታ ተከፋይ፣ ሌሎች የደመወዝ ተቀናናሾች፣ 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር፣ በገዥው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ለሚመለከታቸው ወቅቱን ጠብቆ ያለማስተላለፍ ምክንያት የተፈጠረ ተከፋይ ሲሆን ሂሳቡ በእድሜ ተተንትኖ ሊያዝና በየወቅቱ መከፈል የሚችለውን ሂሳብ ለሚመለከታቸው ሊከፈልና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊከፈል የማይችለው /ባለቤት የሌለው/ ሂሳብ ደግሞ ወደ ሀብትነት ተቀይሮ ስራ ላይ እንዲውል አሳስበናል፡፡

**የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ ሂሳብ፤**

6. በቢሮው የተጠቃለለው የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛን ያላቸው ለመሆኑ በናሙና የተመረጡ ሪፖርት አቅራቢዎች (በከተማ አስተዳደሮች እና ወረዳዎች) የሂሳብ ሪፖርት ሲታይ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የመደበኛ በጀት ሂሳብ ላይ በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣ የተከፋይ እና የተጣራ ሀብት ሂሳብ በድምሩ ብር 9,237,412.18 የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ስለተዘጋጀው አመታዊ ሪፖርት ትክክለኛ መረጃ የማይሰጥና በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣የተከፋይ እና የተጣራ ሀብት ሂሳቦች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ የሪፖርቱን ትክክለኛነት የተዛባና አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡በመሆኑም ምክንያቱን በማጣራት ተገቢው የማስተካካያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ለወደፊቱም የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን ለቢሮው በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑ እየተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡

**በብልጫ ሪፖርት የተደረገ የተጣራ ሃብት ሂሳብ**

7. የተጠቃለለ ፈንድ የሀብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተጣራ ሀብት ብር 9,933,367,073.28 የሚያሳይ ሲሆን ነገር ግን በኦዲት ሲረጋገጥ ወደ 2011 በጀት ዓመት ሊዛወር የሚገባው የተጣራ

ሀብት ብር 9,189,976,499.96 ብቻ በመሆኑ በሪፖርቱ የተላለፈው የተጣራ ሀብት በብር 743,390,573.32 በመብለጥ ተላልፎ ተገኝቷል፡፡

ልዩነቱ በክልል ውስጥ የሌለን ሃብት እንዳለ አድርጎ የሚያሳይ እና በሪፖርቱ መሰረት ውሳኔ የሚያስተላልፉ አካላትን ሊያሳስት የሚችል ነው፡፡ስለሆነም የልዩነቱ ምክንያት በበጀት ዓመቱ የገቢ ተመላሽ ሂሳብ ሊኖር ስለሚችል ለአሁኑ የተደረገውን የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ በማናበብ በሀብት የተከፈለ የገቢ ተመላሽ ካለ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

ቢሮው በሰጠው ግብረ መልስ መሰረት የገቢ እቅድ ክንውንን በተመለከተ ለወደፊቱ የክልሉን ገቢ የመሰብሰብ አቅም ለማጣናከር እና ወጪ የመሸፈን አቅሙን ለማሳደግ የሚያስችል አደረጃጀትና ስልት ከገቢዎች ቢሮ ጋር በመነጋገር በትኩረት የሚሰራ መሆኑን ያሳወቀ ሲሆን በሌሎች ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጅ ለመውሰድ በየደረጃው እየተደረገ ያሉትን ጥረቶች አሳውቋል፡፡

በተለይም በተሰብሳቢ እና በተከፋይ ሂሳብ ላይ መወራረድ የሚችሉት እንዲወራረዱ፣መወራረድ የማይችሉት ደግሞ በስራ ላይ ባለው ከመዝገብ የመሰረዝ መመሪያ መሰረት ምክንያቱን በማጣራትና ማስረጃ በመያዝ የሚሰረዝበት መንገድ ለማመቻቸት በቢሮዎች፣ በክልል ሴክተሮች፣ በዞኖች በወረዳዎች እና በከተማ አስተዳደሮች መ/ቤቶች ስራ እየተሰራ መሆኑንና የተደረሰበትን ውጤት እንደሚገልጽ ቢሮ ክትትል እያደረገ መሆኑን አብራርቷል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ቀጥሎ መ/ቤታችን ከጥር/2011 እስከ ግንቦት 30/2012 ባለው ጊዜ ያከናወናቸው የ270 መ/ቤቶች የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት እና የክትትል ኦዲት ሪፖርት አቀርባለሁ፡፡**

1. መ/ቤቱ በዚህ ሪፖርት ያካተተው የ270 መ/ቤቶች የ2011 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ሪፖርት ውጤት ነው፡ ፡የ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማዕከል 103(38%)፣በዞን 10(4%)፤በከተማ አስተዳደሮች 62(23%) ቀሪዎች 95(35%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡
2. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሠሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡ ከኦዲት ስልት አንፃር ከ270 መ/ቤቶች ውስጥ 231(85.56%) በንሞና እንዲሁም 39(14.44%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማ በመቅረቡ በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡
3. **የኦዲት አስተያየት** የ2011 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 270 መ/ቤቶች መካከል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 221፣ የመጀመሪያ ኢንትሪም ሂሳብ ኦዲት ስራ ብቻ የተጠናቀቀ በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጣቸው 10 መ/ቤቶች ሲሆኑ 39(14%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ስራ በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት መስጠት የማይጠበቅባቸው ናቸው፡፡ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ሲታይ ለ175 (65%) ከዚህ በስተቀር፣ለ2 (1%) አስተያየት መስጠት አልተቻለም፣ለ10(4%) አጥጋቢ አይደለም እና ለ34(12%) ንፁህ የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

   የኦዲት አስተያየቱ ከ2010 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ጋር ሲነፃፀር " **ንፁህ አስተያየት የሚለው**" (በ36%) መጨመሩ በአንዳንድ መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ እና የሀብት አስተዳደር ስርዓቱ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያሳይ ሲሆን፣ "**አስተያየት መስጠት አለመቻል**" ከ1 ወደ 2 ከፍ ማለት የኦዲት ማስረጃዎች አቅርቦት ገደብ እየጨመረ መምጣቱን የሚያመላክት ሲሆን በሌላ በኩል " **አጥጋሚ አይደለም የሚለው**" በከፍተኛ ሁኔታ

መጨመሩ በአንዳንድ መ/ቤቶች የሀብት አስተዳደር ስርዓቱ ድክመት እና በሪፖርት አቀራረብ ላይ ያሉ ጉልህ መዛባቶች እየጨመሩ መምጣታቸውን ያመላክታል። የኦዲት አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ (በ35%) መቀነሱ ባለፉት ቅርብ ዓመታት ህብረተሰቡ ብልሹ አሰራሮችን የመታገል ልምዱ እና ስጋትን መሰረት አድርጎ ኦዲትን የመፈፀም ትኩረት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ወደ ኃላ ዓመቶች የተከማቹ ጥቆማዎች በኦዲት እየተሸፈኑ ስለመጡና በዚህ በጀት ዓመት ከወቅታዊ ወረርሽኙ ጋር በተያያዘ ከሚመለከታቸው አካላት የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ጥቆማዎች መቀነሳቸውንና ስራውም በዚያ መጠን አለመሰራቱን ያመላክታል።

የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና የሙያ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻሉ ጉልህና መሰረታዊ ችግር የተገኘባቸው በመሆኑ "አስተያየት መስጠት አልተቻለም" የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች፡-ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል እና ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸው።

መንግስት የመደበላቸውን ሀብት/ገንዘብ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤ የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፤ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው በመሆኑ "አጥጋቢ አይደለም" የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ደግሞ ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰጭ/ማዕከል፣መቅደላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ህዳር 11 ሆስፒታል፣ኩታበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ደብረ ብርሀን ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት፣መቅደላ ጀግኖች መታሰቢያ ሆስፒታል እና አንነት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸው፡፡

## የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ

4. በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 231 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 58(25.11%) መ/ቤቶች ናቸው። የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እየቀነሰ የመጣ ሲሆን ይህም የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት ሥርዓት ከማጠናከር አኳያ ድክመቶች እንዳሉ የሚያመላክት እና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸው ያሳያል። ምላሽ ያልሰጡ መ/ቤቶችም፤

**ክልል/ማዕከል ተጠሪ**

1. መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዩች ቢሮ
2. አብክመ ፖሊስ ኮሚሽ
3. አብክመ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ
4. አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ማስ/ጽ/ቤት
5. እንጅባራ ጠቅላላ ሆስፒታል

6. ፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል
7. ምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
8. ኮምቦልቻ ግብርና ኮሌጅ
9. ወገል ጤና ማረሚያ ቤት
10. ጃማ ወረዳ ፍርድ ቤት
11. ከሚሴ ማረሚያ ቤት
12. አጣየ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ
13. መቅደላ ጀግኖች መታሰቢያ ሆስፒታል

**ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር**

14. ደምበጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
15. ምዕራብ ጐጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
16. ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
17. ፍኖተ ሰላም ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት

**ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር**

18. አማኑኤል ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
19. ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
20. እነማይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር**

21. ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
22. ጎንደር ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት
23. ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር**

24. ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**አዊ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር**

25. አንከሻ ጓጉሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል
26. ባንጃ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
27. አዊ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ

**ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር**

28. ደሴ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
29. ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
30. አምባሰል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
31. ከላላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
32. መቅደላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
33. አርጎባ ብሄረሰብ ልዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
34. ለጋቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
35. ኩታበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
36. ኮምቦልቻ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት

**አሮሞ ብሄሰብ ዞን አስተዳደር**

37. ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
38. አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
39. ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
40. ባቲ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት

**ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር**

41. ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
42. ጣርማ በር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
43. ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
44. አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
45. ሸዋ ሮቢት ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
46. ደብረ ብርሀን ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
47. አለም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር**

48. መቄት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

49. ቆቦ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
50. ወልድያ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
51. ሀብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
52. ላሊበላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
53. ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
54. ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
55. አንጎት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር**

56. ጋዞ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
57. ዋግ ኽምራ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
58. ሰቆጣ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ናቸው።

## የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

### የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

5. የ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 135,655.46 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 113,605.09 ከቀድሞ ገ/ያገሮች የተገኘ ነው፡፡

   በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር 8 መ/ቤቶች ብር 9,451,672.68 የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ እና በ5 መ/ቤት ቆጠራ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 619,670.04 ተስተውሏል።

ከጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ብር 76,388.49 (56.3%) በክስ ሂደት ላይ እንደሚገኝ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 59,266.97 በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

### የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች

6. በ27 (11.69%) መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2011 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡ (ዝርዝራቸው በዋናው ዘገባ ሪፖርት በዝርዝር ተመልክቷል፡)

## የገቢ ሒሳብ ኦዲት ውጤት

### ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣

7. የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ እቃ/አገልግሎት ሲያቀርብ ለክፍያው የሻት ደረሰኝ/ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበትና ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ማስረጃው እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም በ4 መ/ቤቶች ብር 329,658.79

የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን ተገኝቷል፡-

- **ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 145,550.50 የግብርና ጽ/ቤት ንብረት ለሆነች ተሽከርካሪ የመለዋወጫ ግዥ ተፈጽሞ ለአቅራቢ ድርጅቱ ክፍያ ሲፈፀም፣
- **ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስጭ/ማዕከል ብር** 124,099.26 የመንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ለአንድ አነስተኛ ድልድይ ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ እና የትምህርት ጽ/ቤት 2-ብሎክ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ለተቋራጩ ሲፈፅም፣
- **ባሶና ወራና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 54,009.03 የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት የቢርቢርሳ 1ኛ/ደ/ት/ቤት ግንባታ ለተከናወነበት ከ1ኛ-3ኛ ዙር ክፍያ እና የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በቀይት ቀበሌ የጋራ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ለአከናወነው ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም፣
- **ሽኩዳድ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር** 6,000.00 ለችሎት አገልግሎት የዋለ የህትመት ግዥ ክፍያ ሲፈፀም፣

ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ በስራ ተቋራጮች/በአቅራቢዎች ተወስዶ (ተሰብስቦ) ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ ተቋራጮች ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርገው ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት እያስገነዘብን ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ በሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ በመመስረት ከተጠቃሚው የተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

### ያልተሰበሰበ (በውዝፍ የሚገኝ) ገቢ፤

8. የ2011 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ77 መ/ቤቶች ብር 316,781,111.98 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 149,027,905.87(47%)፣ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር 89,130,782.84(28%)፣ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳዳር ብር 19,174,736.76 (6%)፣ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ብር 17,779,205.25(6%) ፣ ኦሮሞ ዞን አስተዳደር ብር 16,327,284.37(6%) እና ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 14,647,455.67 (6%) ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ::

ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 21/2012 ዓ/ም ድረስ ስለመሰብሰቡ በግብረ መልስ አልተገለፀም፡፡

## ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፣

9. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ44 (16.29%) መ/ቤቶች ብር 29,011,090.57 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ከብር 300,000.00 በላይ ከፍተኛውን የሚይዙት፡-

- ፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል ብር 10,391,244.75 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ጎንደር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 6,948,884.18 የያዙ የገቢ መሰብሰቢ ደረሰኞች፣ደብረ ታቦር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 3,057,831.84 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ፣ሀብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,065,125.22 የያዙ የመደበኛ እና የስፖርት ምክር ቤት ገቢ፣ የእርሻ ስራ እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ ሰቆጣ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 681,974.45 የያዙ የንግድ ስራ ትርፍ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ፣አልቡኮ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 664,960.98 የያዙ የመደበኛ ገቢ፣የስፖርት ም/ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ጋዝጊብላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 361,312.17 የመደበኛ ገቢ እና የስፖርት ምክር ቤት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 408,052.00 የያዙ የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 348,408.00 የያዙ የእርሻ ገቢ ግብር እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ደረሰኝ፣ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 330,873.00 የያዙ የእርሻ ስራ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣የስፖርት ምክር ቤት ገቢ ደረሰኝ እና የመናኸሪያ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ስራ አልቀረቡም፡፡

ለኦዲት ስራ ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ላለመፈፀሙ ማረጋገጥ ባለመቻሉ ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ካሉበት ቀርበው የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት ብር 80,678.30 (0.28%) የያዙ ገቢ ደረሰኞች ብቻ ለውስጥ ኦዲት ቀርበው የተረጋገጡ ስለመሆናቸው በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን በቀሪው የገቢ ደረሰኝ ላይ የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 21/2012 ዓ/ም ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

## የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት

### በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ

10. የ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ102 መ/ቤቶች ብር 2,367,902,413.99 በወቅቱ የፋይናንስ አሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ /ሳይወገድ/ ከመዝገብ ሳይሰረዝ ተገኝቷል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ/የመወራረጃ ወይም የመወገጃ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በቢሮው በቁጥር 6/2004 በክፍል 4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ባሳሰብነው መሰረት ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ 17,540,163.90 (0.74%) ከኦዲት በኋላ የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በቀሪው ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ እስከተሰራበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡

በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በኦዲት ወቅት በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ይሰበሰብባቸዋል ተብሎ ከተያዙ አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ6 መ/ቤቶች ብር 6,854,837.36 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡

ከላይ ከተመለከተው ተሰብሳቢ መካከል በ2 መ/ቤት ብር 2,875,861.57 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣ መቼ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ የሚሳይ ማስረጃ ሳይኖር በደብረ ብርሀን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል እና ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ለሂሳቡ ትክክለኛ ዝርዝር ደጋፊ ማስረጃ ካለ ተጣርቶ በየባለዕዳዎቹ ስም ተለይቶ እንዲያያዝና ክትትል ተደርጐ እንዲሰበሰብ ወይም በመመሪያው መሰረት ከመዝገብ እንዲሰረዝ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ጊዜ ሰኔ 21/2012 ድረስ የተወሰደውን እርምት የሚገልጽ ምላሽ አልደረሰም፡፡

**ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ**

11. በ29 መ/ቤቶች ብር 120,008,450.72 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ በባለቤቱ ስም ተለይቶ በሚያሳይ መልኩ የተመዘገበ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ/ለማስወገድ የማያስችል በመሆኑ የተሻሻለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየስሙ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ከመዝገብ ሊሰረዝ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን ብናሳስብም ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ ብር ብር 380,395.40 (0.32%) ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመኖሩ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

## የወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፤

***የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች***

12. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ12 መ/ቤቶች ብር 9,484,900.60 የተለያዩ የማጭበርበር ድርጊቶች ተፈፅሞበት ተገኝቷል፡፡የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀ መባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ጎንደር ከተማ አስ/ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር መምሪያ ልዩ ኦዲት ብር 8,569,409.63** በከተማ አስተዳደሩ ዋና ዋና መንገዶች ለሚገነባው የውሃ ማፋሰሻ ስራ ግንባታ ለማከናወን በሐሰት ጨረታ የወጣ በማስመሰል፣ቀረቤታ ያለውን ግለሰብ ስሙን በማስቀየር ተቋራጭ በማስመሰል፣የኃላፊ ፊርማ በማስመሰል የክፍያ ማዘዣ በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጎንደር አብይ ቅርንጫፍ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ በሀሰት አሸንፏል በተባለው ተቋራጭ ስም በቼክ ቁጥር 156802435 እንዲተላለፍ በማድረግ በሂሳብ ኦፊሰር ተጭበርብሮ ለግል ጥቅም የዋለ ብር 8,125,000.00፣ በ2009 በጀት ዓመት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጎንደር ከተማ አስተዳደር ለ7ኛ ጊዜ ለተከበረው የኢትዮጲያ ከተሞች ፎረም ፋይናንስና ሎጀስቲክ አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 56/2009 አንቀጽ 13 ተራ ቁጥር 2 ለአንድ የከተሞች ፎረም ተሳታፊ እንዲከፈል ከተፈቀደው በላይ ከመመሪያ ውጭ አለአግባብ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 194,575.00፣በውጭ ሰነድ ላይ ስሙ

በፍሉድ ተሰርዞ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በጽዳትና ተላላኪ ሰራተኛ ስም ወጭ ተደርጎ እንደተከፈለ በማስመሰል ለኃላፊዎች ጥቅም የዋለ ክፍያ ብር 10,000.00፣ በከተማ አስተዳደሩ ለሚከናወነው የኢትዮጲያ ከተሞች ፎረም ስራን ለማቀላጠፍ ተብሎ በከተማው ካሉ የግል የመኪና ባላሀብቶች ጋር የነዳጅ ፍጆታው ከተማ አስተዳደሩ የሚሸፍን ሆኖ ነገር ግን የሹፌር ውሎ አበል ባለተሽከርካሪው እንደሚሸፍን የውል ስምምነት ተወስዶ ወደስራ ከተገባ በኋላ ከዚህ ስምምነት ውጭ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና የቶፐአፕ ክፍያ ብር 26,000.00፣በተመሳሳይ ቀን በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 66,500.00፣የመንገድ ላይ ወንበሮች ስራ ፣የአረንጓዴ ልማት ስራዎች እና የተራራ ላይ ቅርፃ ቅርጾች ስራ ለአከናወነው ሽርክና ማህበር ክፍያ ሲፈጸም የመንግስት የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ሳይደረግ ለግል ጥቅም የዋለ ብር 131,809.63 እና ጎንደር ከተማ ከ2007-2009 ዓ.ም የተሰሩ የውስጥ ለውስጥ መብራት ፖል ስራዎችን በተገባው ውለታ እና በቀረበላቸው የስራ ዝርዝር መሰረት መሰራታቸው ሲረጋገጥ የውስጥ ለውስጥ መንገድ መብራት ፖል ዝርጋታ ሳይከናወን ለተቋራጭ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 15,525.00፣

- **ቃሉ ወረዳ ገ/ኢ/ት/ጽ/ቤት ልዩ ኦዲት ብር 216,495.32** በወረዳው የ022 ቀበሌ የገበሬ ማሰልጠኛ ተቋም ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ያልተሰሩ ስራዎች እንደተሰሩ ተደርጎ በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ ብር 89,922.54፣ ይኸው የግንባታ ስራ የተጓተተ እና የማጠናቀቂያ ጊዜው ያለፈ ቢሆንም በውል ስምምነቱ መሰረት የመልካም ስራ አፈፃጸም ዋስትና ገንዘቡ መወረስ ሲገባው ሳይወረስ ፕሮጀክቱ በመቋረጡ የታጣ የመንግስትን ጥቅም ብር 31,093.23 እና የግንባታ የውል ስምምምነት ያለምንም ምክንያት ተቋርጦ ከተያዘው የውል ዋጋ በላይ አዲስ ውል ተይዞ ለግል ጥቅም የዋለ ክፍያ ብር 42,362.55፣መስክ ሳይወጣ እንደተወጣ በማድረግ በተመሳሳይ ቀን የውሎ አበል በድጋሜ የተከፈለ እና ስልጠና ሳይወሰድ እንደተወሰደ ተደርጎ የተከፈለ ሂሳብ ብር 53,117.00፣
- **ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር 201,494.90** ኤጀንሲው ለጨሞጋ የጁቤ መንገድ ስራ ፕሮጀክት የውሃ ቦቴ ኪራይ ግዥ ለመፈፀም ባወጣው ጨረታ አሸናፊ የሆነው ድርጅት በውል ስምምነቱ መሰረት ባለመፈጸሙ መወረስ ሲገባው አላግባብ ከመመሪያ ውጭ ተመላሽ ተደርጎ ለግል ጥቅም የዋላ የውል ማስከበሪያ ሂሳብ ብር 20,000.00 እና ኤጀንሲው የጋቢዎን ግዥ ለመፈፀም ባወጣው ጨረታ አሸናፊ የሆነው ድርጅት በውል ስምምነቱ መሰረት ባለመፈጸሙ መወረስ ሲገባው አላግባብ ከመመሪያ ውጭ ተመላሽ ተደርጎ ለግል

ጥቅም የዋላ የውል ማስከበሪያ ብር 181,494.90፣

- **እንጅባራ ከተማ አስ/ገ/ኢ/ት/ጽ/ቤት ብር** 165,759.56 የእንጅባራ ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት በከተማው ውስጥ የመንገድ መብራት ጥገና አገልግሎት ለመፈጸም ባወጣው ጨረታ ማስታወቂያ አሸናፊ ለሆነው ተቋራጭ ቅድሚ ክፍያ ዋስትና ሳያቀርብ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ ስራው ሳይሰራ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- **ቤቶች ልማት ድርጅት ጎንደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር** 83,506.23 በጎንደር ከተማ ቀበሌ 17 የሚገኘው የድርጅቱ መኖሪያ ቤት አንድ ከፍል ጥገና ሲፈፀም በተጋነነ ዋጋ ከባለሙያ ግምት በላይ ወጭ ሆኖ የተከፈለ፣
- **ቡሬ ዙሪያ ወረዳ ገ/ኢ/ት/ጽ/ቤት ብር** 64,998.90 በዋና ገንዘብ ያዥ እና በረዳት ገንዘብ ያዥ ስም ቼክ ከተዘጋጀ በኋላ በቼኩ ጀርባ ላይ ገንዘብ ያዦች እንዳስተላለፉለት በማስመሰል የተሳሳተ ፊርማ በመፈረም ገንዘብ ከባንክ ወጭ በማድረግ እና በሂሳብ ኦፊሰር ስም ለመስክ ስራ የተንቀሳቀሱበት በሚል ቼክ በማዘጋጀት ቼክ ፈራሚዎችን በማስፈረም ለመስክ ሳይወጣ በተጭበረበረ ቼክ ለግል ጥቅም የዋለ ክፍያ፣
- **ወረባቦ ወረዳ የቦክክሳ አጠ/1ኛ/ደ/ት/ቤት ብር** 61,873.04 አጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም በጀት ያልተገዙ እቃዎች እንደተገዙ በማስመሰል እና በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ በማድረግ በለቀቀ ተወካይ የግዥ ሰራተኛ እና በወላጆች መምህራን ህብረት ኮሚቴ ሰብሳቢ ስም ፊርማ በማስመሰል ግዥ ሰራተኛ ገንዘብ እንደከፈለ እና ገዝቶ እንዳስረከበ በማስመሰል የሀሰት ሰነድ በማዘጋጀት ወጭው ፀድቆ ለግል ጥቅም የዋለ ክፍያ፣
- **ኮምቦልቻ ግብርና ኮሌጅ ልዩ ኦዲት ብር** 53,174.16 ለኮሌጁ አገልግሎት ሳይውል ተወራርዶ ለግል ጥቅም የዋለ የነዳጅ ሂሳብ፣ ከኖርማላይዜሽን ስሌት ውጭ በብልጫ ተወራርዶ ለግል ጥቅም የዋለ የነዳጅ ሂሳብ እና በተመሳሳይ የጌጅ ንባብ ተወራርዶ ለግል ጥቅም የዋለ የነዳጅ ሂሳብ እና የተሽከርካሪ እጥበት ክፍያ፣
- **ላይ ጋይንት ወረዳ ገ/ኢ/ት/ጽ/ቤት ብር** 26,888.20 አላግባብ መስክ ሳይወጣ መስክ እንደተወጣ ተደርጎ የተከፈለ የውሎ አበል ሂሳብ ፣
- **ላስታ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ብር** 24,610.68 ትምህርት ጽ/ቤቱ በ2006 በጀት ዓመት አጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም በጀት ከትምህርት ቤቶች ግዥ እንዲፈጽም ውክልና ሳይሰጠው ለ58 ትምህርት ቤቶች ባለ4 ጂቢ ፍላሽ በፕሩፎርማ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈጽም ከወቅቱ የገበያ ዋጋ በላይ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈጸመ እና ለግል ጥቅም

የዋለ ሂሳብ፣

- **አዲአርቃ ከተማ መሪ መዘጋጃ ቤት ብር** 11,250.00 የስራ ተቋራጩ መክፈል እያለበት አላግባብ በወረዳው በጀት የተሸፈነ የእንስያ ውሃ ፕሮጀክት የመስመር ዝርጋታ ወጭ፣
- **ደንበጫ ወረዳ ገ/ኢ/ት/ጽ/ቤት ብር** 5,439.98 ተሽከርካሪው አንድ ጊዜ የተጓዘበትን ኪሎ ሜትር በኩፖንና መስክ ላይ ከተቀዳው ነዳጅ ጋር ጨምሮ በድጋሜ የተወራረደ ነዳጅ ወጭ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 3,054,276.23 ተመላሽ የተደረገ፣ብር 534,562.76 በክስ ሂደት ላይ እንደሚገኝ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 5,896,061.61 በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልተገለፀልንም፡፡

## ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ

13. በ12 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 981,019.98 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉ ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በታክሱ ሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ እንዲረጋገጥ ሆኖ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀረት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

## አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ፤

14. በትክክለኛው አሰራር ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ89 (32.96%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 5,678,736.69 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 150,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **አብክመ ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ ብር** 1,017,111.62 ለጉማራ መስኖ ልማት ግንባታ የ3ኛ ዙር እና የቆቦ ወረዳ መስኖ አገልግሎት ስራ የተሰራበት 1ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ከውል በላይ የተፈፀመ፣

- **ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 643,308.40 የአዘዞ ገበያ ማዕከል ለመገንባት ተቋራጩ በወሰደው ውል መሰረት 14ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ከውል በላይ በብልጫ የተከፈለ እና የጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተሞች ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ በከተማው ለሚካሄደው ለ7ኛው የከተሞች ፎረም የመንገድ ዳር መንገድ ዝርጋት ስራ ከተገባው ውል በላይ በብልጫ ለተቋራጩ የተከፈለ፣
- **ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 246,963.93 ለመንገድ ትርንስፖርት ከመደበኛ በጀት ለመንገድ ስራ አገልግሎት የሚውል ኤክስካቫተር ማሽን ኪራይ ክፍያ ሲፈፀም ለተሰራበት 96 ሰዓት ብቻ ክፍያ መፈጸም ሲገባው ለ121 ሰዓት በብልጫ የተከፈለ፣ አስተዳደር ጽ/ቤት ለወሳኝ ኩነት ስልጠና ክፍያ ሲፈጽም በብልጫ የተከፈለ፣የፖሊስ ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ እና መፀዳጃ ቤት ግንባታ የ4ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጽም ለስራ ተቋራጩ በብልጫ የተከፈለ፣ በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ስራ ለሚገኙት መምህራን የሐምሌ ወር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የፀደቀ፣ ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ድጎማ ሲፈፀም በብልጫ የተፈፀመ፣በጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ስራ ለሚከናወኑ የተለያዩ ግንባታዎች ክፊያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ፣ለስልጠና ለተሳተፉ ባለሙያዎች ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ እንደወጡ ተደርጎ እና በድጋሜ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 216,726.56 በወረዳው ውስጥ በተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ እንደወጡ ተደርጎ የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ፣ በተመሳሳይ ቀናት ከተለያዩ የሂሳብ ፕሮጀክቶች በድጋሜ የተከፈለ የውሎ አበል እና በብልጫ የተከፈለ የስልጠና አበል፣ለተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች የጎማ ግዥ ሲፈጸም በብልጫ የተፈፀመ፣
- **አንጎት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 211,329.15 ሰራተኞች መስክ ለወጡበት ክፍያ ሲፈፀም በድጋሜ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣የአሁን ተገኝ 2ኛ ደ/ት/ቤት ቤተ ሙከራ ግንባታ ለተፈጸመበት 2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 167,639.80 መስክ ሳይጣ ቢሮ ውስጥ እና ያመት እረፍት ላይ እያሉ መስክ እንደወጡ ተደረጎ አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣በተለያዩ ወራት ሰራተኞች ለሰሩበት ደመወዝ ሲከፈል በብልጫ የፀደቀ ሂሳብ፣ ለቀጥተኛ ተረጅዎች ክፍያ ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ፣ከተገመተው የካሳ ክፍያ በላይ የተከፈለ፣የመኪና ጥገና ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ፣

- **አብክመ ስፖርት ኮሚሽን ብር 151,257.90** ባህር ዳር አለማቀፍ እስቴዲዮም የመለማመጃ አጥር ለማሰራት ከውል በላይ የተከፈለ ሂሳብ እና ሰራተኞች መስክ ለወጡበት ክፍያ ሲፈፀም በድጋሜ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 150,763.14** ለኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት 3ኛ ዙር የሴቶች ስፖርት ውድድር ለተሰተፉ፣በኮምቦልቻ ከተማ ለተሰጠው የተቀናጀ ማህበረሰብ ተኮር ስልጠና አገልግሎት ለተሳተፉ ባለሙያዎች ውሎ አበል ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ፣ሰራተኞች መስክ ወጥተው ላልሰሩበት ስራ እና በድጋሜ በተመሳሳይ ቀን አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣በብሔረሰቡ ዞኑ የተለያዩ መምሪያዎች ኃላፊነታቸውን ለቀው ወደ ት/ቤት ሲገቡ ሊከፈላቸው ከሚገባው በላይ የተከፈለ ደመወዝ፣የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ወደ ክልል ተዛውረው ሲሄዱ ሊከፈላቸው ከሚገባው በላይ የተከፈለ ደመወዝ፣
- **ሐብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 150,597.56** ሰራተኞች መስክ ወጥተው ለሰሩበት ስራ ክፍያ ሲፈፀም አላግባብ በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል፣የሐብሩ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ለቢሮ አገልግሎት ለተከራየው ቤት ኪራይ ሲከፍል ከውል ስምምነት ውጭ አላግባብ የተከፈለ፣

የ2011 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2010 በጀት ዓመት ብር 7,869,866.10 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ12 ጨምሮ በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 2,191,129.41 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 25,344.50 (0.45%) መተካቱ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ስለመተካቱ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡ ይህም በተለያዩ መንገዶች አላግባብ ክፍያዎችን መፈጸም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከመ/ቤጽ ቁጥር አንጻር እየተባባሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

## የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

15.ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ22(8.15%) በድምሩ ብር 16,313,768.12 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ከዚህም ውስጥ ከብር 400,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- **መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ /SDG/** በሚዳ ኦሮሞ የጻዲቁ ወንዝ ድልድይ ግንባታ ስራ 2ኛ እና 3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የውል ስምምነት ሰነድ እና የቅድሚያ ክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብ የተከፈለ ብር 2,724,679.34፣

- **ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አዲሱ የወገል ጤና መናህሪያ ግንባታ 1ኛ ዙር ክፍያ እና በተለያዩ ቀበሌዎች ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተገነቡ መፀዳጃ ቤቶች የተለያዩ ዙር የግንባታ ክፍያዎች፣ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት በመደበኛ በጀት ከአስገነባው የወገል ጤና መናህሪያ የመጨረሻ ዙር ክፍያ፣ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፐራይዞች ልማት ጽ/ቤት በ02 ቀበሌ ላስገነባው ሸድ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 2,497,132.25፣
- **ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ** በሰሜን ወሎ ዞን በሀብሩ ወረዳ አንጦ ጨፌ ቀበሌ 34 ለያሰራው የወተት ላሞች ሸድ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የግንባታ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ እና ለክምር ድንጋይ ቴክኒክና ሙያ አገልግሎት የሚውል ትራንስፎርመር ግዥ ሲፈፀም በኢትዮጲያ ኤሌትሪክ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የዋጋ ግምት ሳይቀርብ የተከፈለ ክፍያ ብር 1,922,097.95፣
- **ትምህርት ቢሮ** በቃሉ ወረዳ ት/ጽ/ቤት የ2ኛ ደረጃ እያስገነባ ላለው ግንባታ ለተቋራጭ ማህበራት 1ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የግንባታ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 1,793,534.65፣
- **ባሶና ወራና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የወረዳው ምገድና ትራንስፖር ጽ/ቤት ከመደበኛ በጀት ከሐሮ እስከ አማን ጉለት ያለው መንገድ ሲጠገን 1ኛ እና የመጨረሻ ዙር ክፍያ፣ ከአባሞቴ እስከ ናስ ያለው መንገድ ሲጠገን 1ኛ እና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ብር 1,554,354.50፣
- **ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የትምህርት ጽ/ቤት ከመደበኛ በጀት ሂሳብ ለእነዋሬ ሚሊኒየም አጠ/2ኛ/ደ/ትቤት ግንባታ 2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ብር 1,379,912.87፣
- **አብክመ ስፖርት ኮሚሽን** ተጨማሪ የስራ ውል ስምምነት ሳይደረግ 51ኛ ዙር ክፍያ ለኮንትራክተር ሲፈፀም የግንባታ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 795,671.65
- **አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ከካፒታል በጀት የአጼ ሚኒሊክ መታሰቢያ ሙዚየምና የባህል ማዕከል የዙሪያ አጥር ግንባታ ሲከናወን የግንባታ ስራ ዝርዝር ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 699,715.20፣
- **ግብርና ቢሮ** በላይ ጋይት ወረዳ የጥጆ ወንዝ የካናል ስራ፣ በሰቆጣ ከተማ ጢጦ አነስተኛ ግድብ ስራ፣ በሳሃላ ወረዳ ፃድብቃ አነስተኛ ግድብ ግንባታ ስራ፣በሃገረ ማርያም ወረዳ በዛላ ወንዝ ለሚሰራው የወንዝ ጠለፋ ስራ ፣በደንበጫ ዙሪያ ወረዳ ዋድ አዲስ አለም ቀበሌ ለሚገነባው የገብያ ማዕከል ግንባታ ፣በፈለገ ብርሃን ቀበሌ ለሚገነባው የገብያ ማዕከል ግንባታ ክፍያ ሲፈጸም የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈጸመ ብር 605,653.07፣
- **ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የቃሚ እና የቆፓሮ ካናል ስራ ግንባታ ሲከናወን የ1 እና 2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 515,723.10 ናቸው፡፡

ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት /የክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ ሳይቀርብ እና ርክክብ ሳይፈፀም ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 18,995.63 (0.12%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

## ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ

16. ማንኛውም ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ25 (9.26%) መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 10,571,713.53 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 75,726,827.04 ጋር ሲነፃፀር በ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በ7 እና በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 65,762,820.44 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ መ/ቤቶች ከችግሮቻቸው እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ቢያመላክትም በአንዳንድ የክልል ቢሮዎች ግን ችግሩ ገዝፎ ታይቷል፡፡ ስለሆነም ክፍያውን የፈፀሙት መ/ቤቶች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን ማስረጃው የማያመላክት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት ያሳሰብን ቢሆንም ከኦዲት በኋላ ማስረጃ የቀረበለት ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

## ሙሉ ማስረጃቸው ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻሉ የወጪዎች፤

17. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ15 (5.56%) መ/ቤቶች ብር 23,289,728.40 የያዙ የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከኦዲት በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር ተረጋግጦ በግብረ መልስ እንዲገለጽ ብናሳስብም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡ ከፍተኛ ወጪ ይዘው ማስረጃ

ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከልም ከብር 1,000,000.00 በላይ ማስረጃ ያላቀረቡ መ/ቤቶች፡-

- ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 6,247,298.16፣
- አንጎት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 4,828,817.11፣
- ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,226,204.91፣
- ሐብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,102,986.86፣
- አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,898,5,284.00
- ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,594,620.14 ናቸው፡፡

ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ድርጊት አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ይሁንና ስለተወሰደው እርምጃ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 21/2012 ድረስ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡

**የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሒሳብ**

18. የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱ እና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ76(28.15%)መ/ቤቶች ብር 29,254,400.10 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም የግዥ አፈጻፀም ችግር ጎልቶ የታይባቸው ከብር 1,100,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- **ደቡብ ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 2,525,002.33** ለተለያየ ሴክተር መ/ቤቶች የጽዳት እና የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሲፈፀም ህጋዊ የውል ስምምነት ሳይኖር የተፈጸመ ግዥ፣ለሚሊሻ ጽ/ቤት የመኪና መለዋወጫ ግዥ ሲፈጸም በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ፣ትምህርት መምሪያ ኮምባይን ዴስኮችን ግዥ ሲፈጽም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈጸመ ግዥ፣
- **ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 2,450,046.28**፤ ፍትህ ጽ/ቤ እና ፍርድ ቤት የቢሮ ግንባታ በጨረታ መፈፀም ሲገባው በወረዳው ጥቃቅንና አነስተኛ ለተደራጁ ኢንተርፕራዞች ልማት ማህበራት ያለምንም ውድድር አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር ከግዥ መመሪያው ውጭ በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ ግዥ፣ለጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ጥገና ሲፈጸም በግልጽ ጨረታ

መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣የግንባታ ማቴሪያል ግዥ ሲፈጸም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት የተፈጸመ ግዥ፣

- **ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 1,846,944.68 በወረዳው የተለያዩ ቦታዎች ለሚሰራው መንገድ ቆረጣ እና ጠረጋ ስራ የኤክካቫተር እና ዶዘር ኪራይ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳቀርብ በውስን ጨረታ የተፈጸ ግዥ፣
- **ደራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 1,380,052.22 ለወረዳው የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ለተሽከርካሪ መለዋወጫ፣ዲኮር እና ጥገና ግዥ፣ የግንባታ እቃዎች ግዥ፣የፕሪንተርና ኮፒተሮች ጥገና ግዥ፤ የጀነሬተር ግዥ፣ ስሚንቶ ግዥ፣የውሃ ማጠጫ ፕላስቲክ ግዥ፣የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች ግዥ፣የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ሲፈጸም በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ፣
- **ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 1,108,662.58 አስተዳደር ጽ/ቤት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ፣ መንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት የካሜራ ግዥ በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ ግዥ፣
- **ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 1,105,809.75 ለተለያ ሴክተር ጽ/ቤቶች የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ግዥ፣ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣የግንባታ ግብዓት ግዥ ሲፈጸም በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ፣
- **ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 1,102,798.53 ከውሀ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ከመደበኛ በጀት ላይ ለጨሌ ቀበሌ የውሀ መስመር ዝርጋታ የሚውል የቧንቧ መገጣጠሚያ እና ቧንቧ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ የሚሉት ከ1.1 ሚሊዮን በላይ የግዥ አፈጻጸም ግኝት የተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለው የግዥ መመሪያውን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች ባሳሰብነው መሰረት ለብር 586,898.70 ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ከተገኘው ግብረ መልስ መረዳት የተቻለ ሲሆን በቀሪው ግኝት ላይ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 21/2012 ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2010 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 69,982,706.37 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ40 እና በገንዘብ መጠን በብር 40,728,306.27

ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል አፈፃፀማቸው በአንፃራዊነት የተሻለ እንደነበር ያመላክታል፡፡

**የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ፤**

**በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ፤**

19. የ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ97 መ/ቤቶች ብር 1,114,129,856.19 ተከፋይ ዕዳ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅት የፋይናንስ መመሪያውን ተከትሎ ሳይከፈል ተገኝቷል።

በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር ያለበት ተከፋይ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 652,805,367.12 ጋር ሲነፃፀር በ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር በ12 እና በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 461,324,489.07 ጨምሮ ተገኝቷል። ይህም በወቅቱ ያልተከፈለ ዕዳ ክምችት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች እየጨመረ መሄዱን ያመለክታል። በወቅቱ ያልተከፈለ ከብር 20 ሚሊዩን በላይ ከፍተኛ የተከፋይ ሂሳብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል፡-

- ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 413,587,289.31፣ትምህርት ቢሮ ብር 52,839,920.95፣ ደቡብ ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 52,759,163.49፣ ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 48,121,443.83፣መንገድ ኮንስትራክሽ ኤጀንሲ ብር 44,219,620.28፣ግብርና ቢሮ ብር 41,691,736.41፣ ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 36,954,283.70፣ዋግኽምራ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 27,756,707.94 እና ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 25,670,751.00 ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተከፋይ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመክፈያ ጊዜ ያላቸው ወይም ወደ ተጣራ ሀብት የሚቀየሩበት ሁኔታ ይህ ካልተቻለ በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ብናሳስብም ከኦዲት በኋላ ለባለጥቅሙ የተከፈለ ወይም ተገቢው እርምጃ ስለመወሰዱ ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ ተከፋይ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም።

**ከላይ ከተመለከተው ተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

20. የ2011 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ30 መ/ቤቶች ብር 40,374,934.81 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቼ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል።

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቼ እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል

እየተደረገ በየባለቤቱ ተለይቶ መመዝገብ ወይም ለሚመለከተው መከፈል ካልቻለም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር እንዳለበት በሪፖርታችን ባሳሰብነው መሰረት ብር 224,336.02 (0.56%) ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ስለመሆኑ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ በግብረ መልስ አልተገለፀም፡፡

## የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት

21. የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፣ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 231 መ/ቤቶች መካከል በ88 (38.10%)መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች በማረም ሊከሰት የሚችለውን ከፍተኛ የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፣ አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

## የንብረት ሂሳብ ጉድለት

22. ሂሣባቸው በልዩ ኦዲት ከተደረጉ 2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 116,482.50 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ጉድለት/ማጭበርበር የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር፡-

- **የወገል ጤና መቻሬ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ብር 76,929.67** በፕሮጀክቱ ንብረት ኦፊሰር ሆነው ከ10/2/2002-05/9/2006 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የንብረት ሂሳብ ጉድለት እና 7-ዓይነት ዋጋቸው ያልታወቁ ንብረቶች፣
- **የገጠር መንገድ ኮንስትራክስን ኤጀንሲ ብር 39,552.83** የንብረት ክፍል ሰራተኛ የነበሩት 17/9/2001-15/2/2005 ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት ጉድለት ናቸው፡፡

በመሆኑም ከንብረት ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም ገና በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በምላሹ አልተገለፀልንም፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ያለፈው ዓመት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ኦዲት ሪፖርት፤**

23. የ2011 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን መደበኛ ኦዲት በተደረጉ 231 መ/ቤቶች በተደረገው ያለፈ ዓመት ግኝቶች የክትትል ኦዲት በ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርገው በተገኙ ግኝቶች ላይ በተቋማት ያለው የማሻሻያ እርምት እርምጃ አወሳሰድ ሲጣራ በ27 መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ቀን ሰኔ 21/2012 ዓ.ም ድረስ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው የኦዲት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. **ላሊበላ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 9,897.60 እና በብልጫ የተፈፀመ ወጭ ብር 1,030.00፣
2. **አርጎባ ብሄረሰብ ልዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በብልጫ የጸደቀ ወጭ ብር 213,434.00፣ አላግባብ የተፈጸመ ወጭ ብር 28,462.00 እና ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንግድ የተፈጸመ ግዥ ብር 4,115.00፤
3. **ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 87,023.70 እና በድጋሜ የተከፈለ ወጭ ብር 10,000.00 እና በብልጫ የተፈፀመ ወጭ ብር 2,279.90፣
4. **ደ/ኤልያስ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 14,042.00፣
5. **እነማይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 18,060.00፣ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የስፖርት ም/ቤት ገቢ ደረሰኝ ብር 98,717.00 እና ጊዜያዊ ርክክብ ሳይፈጸም የተከፈለ ክፍያ ብር 460,473.63፣
6. **ገንዳ ውሃ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 10,532.00፣ገንዘቡን ለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 15,935.00 እና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳቀርብ የተፈፀመ ግዥ ብር 196,452.50፣
7. **አምባሰል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ኢኮኖሚያዊ ባለሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ 284,500.58 እና ገንዘቡን ለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 116,844.90፣
8. **ለጋንቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 10,901.05 እና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳቀርብ የተፈፀመ ግዥ ብር 38,300.00፣
9. **ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 42,070.85፣
10. **አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 13,288.00፣

11. **እንጅባራ ጠቅላላ ሆስፒታል** አላግባብ የተከፈለ የቤት ኪራ ሂሳብ ብር 63,199.66፣
12. **ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበልና ስልጠና አበል ብር 27,406.00፣
13. **ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የጥሬ ገንዘብ እና የመድህኒት ሂሳብ ጉድለት ብር 11,296.69 እና ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 101,428.60፣
14. **ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በውለታው መሰረት ያልተሰበሰበ ያቅርቦት መዘግየት የቅጣት ገቢ ብር 73,030.57፣ የግንባታ ስራ ስፍር ልኬት ወረቀት (ፒይመንት ሰርተፍኬት) ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 1,493,525.52 እና ገንዘቡን ለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 46,971.55፣
15. **ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 54,700.00፣በብልጫ የፀደቀ ወጭ ብር 193,677.68፣በውለታው መሰረት ያልተሰበሰበ ያቅርቦት መዘግየት የቅጣት ገቢ ብር 11,809.32፣ ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 56,011.62፣ እና የመደበኛ ወጭ ማስረጃ ብር 8,523,496.86፣የግንባታ ስራ ስፍር ልኬት ወረቀት(ፒይመንት ሰርተፍኬት) ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 137,571.00 እና ገንዘቡን ለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 152,616.03
16. **ደንበጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በውለታው መሰረት ያልተሰበሰበ ያቅርቦት መዘግየት የቅጣት ገቢ ብር 38,007.31፣
17. **ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብልጫ የፀደቀ ወጪ ብር 40,770.13፣የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 115,720.51፣ በውለታው መሰረት ያልተሰበሰበ ያቅርቦት መዘግየት የቅጣት ገቢ ብር 10,879.84፣ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የመደበኛ እና ስፖርት ም/ቤት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 231,303.00 እና የመደበኛ ወጭ ማስረጃ ብር 3,292,654.22፣
18. **አይከል ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ያለግንባታ ማስረጃ ተፈጸመ ወጭ ብር 952,712.30
19. **ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ገንዘቡን ለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 86,439.50፣
20. **ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ገንዘቡን ለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 15,542.24 እና አላግባብ የተከፈለ የግንባታ ማሽን ኪራይ ብር 21,514.17፣

እነዚህ በእያንዳንዱ የግኝት እርዕስ ከብር 10,000.00 በላይ የሆኑ በ20 መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች በወቅቱ በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሜ ያሳወቅን ሲሆን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጠናከር መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና የፍትህ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራውን የክትትል ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የእርምት እርምጃ በማይወስዱ እንዲሁም ምላሽ በማይሰጡ አካላት ላይ በህግ አግባብ እንዲጠየቁ የሚሰራ ይሆናል፡፡

- በተለይም አላግባብ/በብልጫ/ላልተሰራ ስራ የተከፈሉ ውሎ አበል እና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 1,319,063.29 ከሚመለከታቸው አካላት ላይ መተካት ሲገባው ይህ አለመፈፀሙ የተጠያቂነት አሰራሩ የላላ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ጉዳዩን መከታተል እና የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚገባቸው አካላት በህግ ሊጠየቁ ይገባል፡፡
- ለኦዲት ስራ ሳይቀርቡ እና በውስጥ ኦዲተር ሳይረጋገጡ የቀሩ ወጭ የተፈፀመባቸው የወጭ ማስረጃዎች ብር 11,816,151.08 እና የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈፀመ ወጭ ብር 3,044,282.45 ላይ የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱ የሚያስጠይቅ እና ተግባሩም ለሌሎች ተቋማትም መልካም ያልሆነ ማሳያ ሆኖ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመ ባለመታወቁ ከፍተኛ ስጋት የሚያሳድር በመሆኑ ተከታትለው ተገቢ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ በነበረባቸው አካላት ላይ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በእርምጃ አወሳሰድ መጓደል ምክንያት ለመንግስት ገቢ ያልሆነ ገንዘብ እና እርምጃ ያልተወሰደበት ግኝት አሁንም በትኩረት ተይዞ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ሪፖርቱ የደረሳቸው ሁሉ (የህግ አካላትን ጨምሮ) ሊከታተሉ ይገባል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡**

**የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት፤**

24. የ2011 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛነት ኦዲት ተደርገው የኦዲት አስተያየት ከተሰጣቸው 221 መ/ቤቶች ውስጥ ለ34 (12%) ***"ንፁህ"*** የሚል የኦዲት አስተያየት እንዲሁም 175 (65%)**"ከዚህ በስተቀር"** የሚል ኦዲት አስተያየት ያገኙ ሲሆን **‹‹አስተያየት መስጠት አልተቻለም››** እና **‹‹አጥጋሚ አይደለም››** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች ብዛት ውስን በመሆኑ ሁሉም የተሻለ አስተያየቶችን እንዲያገኙ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ቢጠበቅም አብዛኞቹ የክልላችን መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት አድርገው በጀትን ለመምራት ጥረት እያደረጉ መሆኑን ያመላክታል፡፡

**ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት**

25. የ2011 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት የተደረጉ ተቋማት በምላሽ አሰጣጥና የእርምት እርምጃ አወሳሰድ ረገድ ከዓመት አመት እየቀነሰ ይህም የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት ሥርዓት ከማጠናከር አኳያ ድክመቶች እንዳሉ የሚያመላክት እና የሚጠበቀውን ያሕል ለውጥ እየታየ ባለመሆኑ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸውና በዚህም ላይ ያለው የተጠያቂነት ሰርዓት የላላ መሆኑን ያሳያል፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት**

26. የ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 135,655.46 ጉድለት የተገኘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ8 መ/ቤት ብር 9,451,672.68 የቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ የተገኙ እና በ9 መ/ቤት ቆጠራ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 619,670.04 የተገኘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2011 ዓ.ም ላይ በ27 መ/ቤቶች ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በመ/ቤቶቹ አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ ያልተሟላ በመሆኑ በኦዲት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

ይህም በጥሬ ገንዘብ አያያዝ ስርዓት መሰረት የመፈፀም ክፍተቶች እንዳሉና የጥሬ ገንዘብ ኦዲት እንዲሰራ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ያላሟላ አሰራር በበርካታ መ/ቤቶች የሚስተዋል መሆኑን ያሳያል፡፡

**የገቢ ሂሣብን በተመለከተ**

27. የ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መካከል በ2 መ/ቤቶች ብር 329,658.79 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ በመፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን የተገኘ ሲሆን በ77 መ/ቤቶች ብር 316,781,111.98 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ በውዝፍነት ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሚልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ44 (16.29%) መ/ቤቶች ብር 29,011,090.57 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይህም መንግስት ላቀደው ዓላማ ማዋል የሚችለውን ገቢ በዚህ ሁኔታ አለመሰብሰቡ እና ለኦዲት ያልቀረበት ደረሰኞች መኖራቸው በገቢ አሰባሰቡ እና መረጃ ይዞ ለኦዲት በማቅረብ በኩል ክፍተቶች መኖራቸውን ያሳያል፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት**

28. የ2011 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች ውስጥ በ102 መ/ቤቶች ብር 2,367,902,413.99 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡ በ6 መ/ቤቶች የ3ተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 4,090,515.54 መገኘቱ፣በ2 መ/ቤት ብር 2,875,861.57 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣መቸ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ እና በ29 መ/ቤቶች ብር 120,008,450.72 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት መገኘቱ በተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝና በመመሪያው መሰረት ከመፈጸም አንጻር ክፍቶች ያሉና በሂደትም ያለመሰብሰብ እድሉን እንደሚያሰፌው ያሣያል፡፡

**የወጪ ሂሳብን በሚመለከት**

29. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ12 መ/ቤቶች ብር 9,484,900.60 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ መገኘቱ እና በ12 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 981,019.98 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት

የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ89(32.96%) መ/ቤቶች ለተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥዎች እና አላግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች በድምሩ ብር 5,678,736.69 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው ይህ ባለመደረጉ በ22(8.15%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 16,313,768.12 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

በ25 (9.26%) መ/ቤቶች የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 10,571,713.53 የወጪ ደረሰኝ /ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና ተመዝግቦ መገኘቱ፤ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ15(5.56%) መ/ቤቶች ብር 23,289,728.40 የያዘ የክፍያ ማስረጃ ለኦዲት ሳይቀርብ መቅረቱ፤የዕቃዎች አገልግሎቶች የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ በ76 (28.15%) መ/ቤቶች ብር 29,254,400.10 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓትን የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም የአንዳንድ መ/ቤቶች የወጪ አፈፃፀም ህግን ያልተከተለና ለግል ጥቅም ለማዋል ክፍተቶች የፈጠረ አፈፃፀም የተከተሉ መሆኑን ያመላክታል፡፡

### የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት

30. የ2011 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ97 መ/ቤቶች ብር 1,114,129,856.19 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅት ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጠራ ሀብት ያልተቀየረ ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን በ30 መ/ቤቶች ብር 40,374,934.81 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ይህም መንግስት ትክክለኛ ዕዳውን አውቆ በወቅቱ እንዳይከፍል ወይም ባለቤት የሌለውን ሂሳብ ወደ ሀብትነት ቀይሮ እንዳይጠቀም ያደረገው መሆኑን ያሣያል፡፡

### የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ

31. የ2011 በጀት ዓመት ሒሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 231 መ/ቤቶች መካከል በ88(38.10%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ሲቀር በልዩ ኦዲት ከተደረጉ መቤቶች ብር 116,482.50 በጉድለት ከመገኘቱም በላይ የንብረት ኦዲትን በመደበኛው አሰራር መሰረት ኦዲት ለማድረግ የሚያሳችል ማስረጃዎች በመያዝና የተዘረጉ አሰራሮችን በተሟላ መንገድ ባለመፈፀም የንብረት ኦዲት እንዳይደረግና ተጠያቂነት እንዳይጠናከር አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠሩን ያሣያል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፡፡**

በዚህ በጀት ዓመት ባቀረብነው የመ/ቤታችን ዕቅድ አፈፃጸም ላይ የተስተዋሉ ውስንነቶች፣ በኦዲት ተደራጊዎች የታዩ ግኝቶች ተሻሽለው የኦዲት ሽፋናችን እንዲያድግ፣የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር አመራር ሥርዓት መጠናከር እንዲችል እና የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጎለብት የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያቶች አቀርባለሁ፡፡

**የኦዲት ሽፋንን ለማሳደግ ጥራቱን እና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ለማድረግ ከአደረጃጀት አንጻር ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡**

32. በክልላችን ያለው ልማት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐለበት በመምጣቱ የኦዲት ተደራጊ ተቋማት ብዛትና በጀት እየጨመረ የሚገኝ በመሆኑ የኦዲት ሽፋንኑን ማሳደግን አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ሪፖርት ማቅረብ ወሳኝ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይም ማህበረሰቡ ስለ ኦዲት ሙያ ግንዛቤ በመያዙና የጥቆማ ተሳትፎው በመጨመሩ እንዲሁም ለፍትሃዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሲባል በየደረጃው ካሉ ፍርድ ቤቶች፣ በፍትህ አካላት እና በስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች በስፋት እየቀረቡና በተለየ ትኩረት ተይዘው ካልተሰሩ አሁን ባለው አደረጃጀት ከመደበኛው ኦዲት ስራ ጋር ተደርበው የሚሰሩ በመሆኑ ለጥያቄው ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ያላስቻለ ከመሆኑም በላይ ከስራው ጥራት አንጻር ሰፊ ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ በመደበኛ ኦዲት እቅድ አፈጻፀም ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ በመሆኑ የመ/ቤቱን አደረጃጀት ማሻሻል አስፈላጊ አድርጎታል፡፡

ይኸውም የልዩ ኦዲት ስራ ከባህሪው፣ ካስቸኳይነቱና በህግ ፊት ለቀጠሮ የሚፈለግ መሆኑ፣ ጊዜ የማይሰጠው ስራ በመሆኑ የመደበኛ ስራውን ሊያስቆም በሚችል ደረጃ ጫና እያስከተለ በመምጣቱ የመ/ቤቱን የእቅድ አፈፃፀም ለማሻሻል አደረጃጀቱ ምላሽ እንዲያገኝ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡**

33. ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ፣ በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት

በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ላይ በየደረጃው በሚገኙ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና የፍትህ አካላት አማካኝነት ክትትል ሊደረግበት እንዲሁም የኦዲት እርምጃ አወሳሰድ ክትትልና ድጋፍ ግብረ ኃይል በየደረጃው በማቋቋምና በማጠናከር የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

ይህን ክትትልና ተጠያቂነት ለማጠናከር በመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዩች ቋሚ ኮሜቴ (Public Accounts Committee-PAC) በክልሉ ምክር ቤት መቋቋም ይችል ዘንድ ከፌደራልና ከሌሎች አቻ ክልሎች የተወሰደው ልምድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ነው፡፡**

34. በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተሟላና ህጋዊ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ አቋቁሞና አስተካክሎ በመመዝገብ እና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያገናዘቡ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳያችሁት ታታሪነትና የሙያ ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

የሽመቤት ደምሴ (ዶ/ር)

ዋና ኦዲተር

ሰኔ/2012 ዓ.ም

<u>**ባህር ዳር!!**</u>